ላይ አብረው በርካታ ጦርነቶችን በጀግንነት ተዋግተዋል። እስካሁን እንዳደረጉት ያለፈውን መከፋፈላቸውንና መጋጨታቸውን ረስተው በጋራ በሚያስተሳስሯቸው እሴቶች ላይ በማተኮር ወደፊት በስምምነት፣ በእኩልነት፣ በመከባበር፣ በኩራት እና ክፍ ባለ አስተሳሰብ አብረው ለመኖር መቻል አለባቸው። በሰላምና ብልጽግና ጎዳና ለመጓዝ ያለፈውን ቅሬታ መቆፈር ሳይሆን በመጪው ብሩህ ተስፋ ላይ ማተኮር ነው የሚያስፈልገው።

ባመዛኙ በማርክሳውያንና በዳርዊናውያን ተጽዕኖ ምክንያት እኔና የኔ ትውልድ በእግዚአብሔር መኖር አናምን ይሆናል። እንደዚህ ብናስብም መብታችን ነው። ሆኖም በእግዚእብሔር መኖር የሚያምኑትንና ህይወታቸውም በፈጣሪያቸው ዙሪያ የተሽከረከረውን የእባቶቻችንን እውነታ ቅንጣት ታህል አይለውጠውም። የሳባ ንግሥት ራስዋን ንግሥተ-ነገሥታት ብላ ከመጥራቷ በፊት ሁሉም የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥቶች ባንድ ጊዜ ንጉሦችም ሊቀ-ካህናትም ነበሩ። በዚህም ምክንያት ፈሪሃ-እግዚእብሔር በየልቦናቸው ያደረ፣ ባመራራቸውና በፍትህ አሰጣጣቸው ህቀኞች፣ ፍርድ አስተካካይዎች እና ቸሮች ሆነው ያለፉ ነበሩ። ታሪካቸው ይህንን ሀቅ ያረጋግጣል። ለኛ እምነት እንዲገጥም ብለን ይህንን እውነታ ልንቀይረው አንችልም። እንቀይር ብንልም እርባናቢስነት ነው። የዚያ እውነታ ውጤቶች በመሆናችን በዛሬው እኛነታችን ላይ የሚያሳርፈውን ተጽእኖውን ልናስቀይረው የማንችለው ያለፈ ታሪካችንን ትምህርት አድርገን ልንቀበለው ይገባል። በነዚህ ዓመታት ሁሉ ስለ ታሪካችን እውነታውን ተነፍገን በጨለማ ውስጥ ኖረናል። ይህ ጨለማም በላያችን ላይ ሊሰላ የማይችል ጉዳት፣ ጥፋት፣ ውድመት፣ ስቃይ፣ መከራ እና ቁጣ አድርሶብናል። ሀቁን ማወቂያና ነፃ መውጫ ጊዜ አሁን ነው። እኔ በበኩሌ የአባቶቻችንን እና የናቶቻችንን ሽጋውን ውርስና ቅርስ አፈቅራለሁ፣ አከብራለሁ፣ እንከባከባለሁ። ራሴንም የዚያ ውርስና ቅርስ እንድ አካል አድርጌ እቆጥራለሁ። ያባቶቼንና የናቶቼን ታሪክ የዛሬውን ማንነቴን ይበልጥ እንዳውቅና እንዳደንቅ ያደርገኛል። ያለፈው ያባቶቼና የናቶቼ ክብርና ዝና ወኔዬን እንዳድስና በወቅታዊ ችግሮቼ ሳቢያ በንቀት በምትመለከተኝ በዚች ዓለም ውስጥ ለራሴ ያለኝን ክብር ከፍ አድርጌ እንዳይ ያደርገኛል።

በምዕራብ አገራት ለበርካታ ዓመታት የኖረ አንድ አሮሞ ጓደኛዬ ‹‹ኢትዮጵያ›› የሚለው ስም አይመቸውም። ኢትዮጵያ በነበረበት ወቅት ባዳበረው ዘረኝነት ወይም ስላለፈው የኦሮሞ ታሪክ በለማው ወይም ባነበበው በጥላቻ የተሞላ መራራ አፈ-ታሪክ የተነሳ በግሉ በኢትዮጵያ ላይ፣ በሰንደቅ ዓላማዋና ከኢትዮጵያ ጋር በተያያዘ በማናቸውም ነገር ላይ ጥላቻና ንቀት አድሮበታል። እየቆየም በጣም ስሜታዊ እየሆነ መጥቷል። ይህ ከቁጥጥር የወጣ የስሜት ግንፈላውና ምሬቱም ኢትጵያዊነቱን እስከሚጠላና እስከሚክድ ድረስ የማገናዘብ ችሎታውን አጥፍቶበታል። ምንም እንኳ አያት-ቅድመ አያቶቹ ለኢትዮጵያ ስልጣኔና ነጻነት ብዙ ያበረከቱ ኩሩ እና የተከበሩ አሮሞዎች ቢሆኑም ቅሉ እሱ ግን ኢትዮጵያዊነቱን የጠላና የካደ ሰው ሆኗል። ይህ መቸም አሳዛኝ ድምዳሜ ነው። በጤናማ አእምሮው በሚሆንበት ጊዜ ግን ኢትዮጵያዊ መሰረቱን ይቀበል ይሆናል። ይለማው የነበረው ማንኛውም ኢፍትሃዊ የሆነ ስሜት ሁሉ ዝርያዎቹ በሆኑ በአሮሞዎች ነገሥታት እና ንግሥተነገሥታት በሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ ሁሉ በግድ የተጫነባቸው መሆኑን ሲረዳ ለዛሬዋና ለነገዋ ኢትዮጵያ የተሻለውን መንገድ ለመጥረግ ጥረት ማድረጉ አይቀርም።

የኔን ጉዳይ እንደ አብነት እንውሰድ፤ በሺዎች የሚቆጠሩ አማሮች በቤንች ማጂ እና በቤንሻንጉል ዞኖች ከመሬታቸውና ከመኖሪያቸው ያለ አግባብ ሲፈናቀሉ፤ መሬታቸው፣ ንብረታቸው እና ገንዘባቸው (ይህ ርዕስ በሚጻፍበት ወቅት በፌደራሉ መንግሥት ታስረው በመመርመር ላይ ባሉ) በአካባቢው ባለስልጣኖች ሲወረስባቸው በጣም አዝኜ ነበር። ደርግ ሥልጣን ከያዘበት ከዛሬ 40 ዓመት ጀምሮ አማሮች ስለተገለሉ እና ሥልጣን አልባ ስለሆኑ ለማንም ስጋት አለመሆናቸውን አውቃለሁ። ይህንን ኢ-ፍትሐዊነት በመቃወም አንድ ግጥም ጻፍሁ። ለተበደሉ አማሮች መቆርቆሬን ያልወደደ አንድ ሰው ኦሮሞነቱን አስታውሶ ሙልጭ አድርጎ በኢ-ሜይል ሰደበኝ። በጋጠወጥነትም እንዲህ አለ፡- ‹‹ከተማረ ጋላ መሀይም ጉራጌ ይሻላል›› ይህን የጻፈው ትክክለኛ ስሙን ደብቆ ነው። እንዲህ ስል በጥሞና ጻፍኩለት፡- ‹‹እባክህ መሀይም ጉራጌ ከተማረ ጋላ መብለጡን በማስረጃ አረጋግጥና አሳምነኝ፤ ይህን ማድረግ ካልቻልክ ከሰብአዊነት ደረጃ ዝቅ ያልክ ተራ እንስሳ ነህ። ንግግርህ አሮሞዎችን ብቻ ሳይሆን ብልሆቹን ወገኖቻችንን ጉራጌዎችንም ያዋርዳል።

ኢትዮጵያውነትህን እጠራጠራለሁ›› በርግጥ የማይረባ ዘለፋውን እንዴት እድርጎ በማስረጃ ያስደግፈው? ዝም ብሎ ኦሮሞነቴን እየጠቀሰ መሳደቡን ቀጠለ፡፡ ከስድቦቹ መሃል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡

‹‹የእርማጌዶን ምልክቱ

ኦሮሞ ቅኔ ልዝረፍ ማለቱ››

ከምርጥ የግዕዝ ባለ-ቅኔዎች ውስጥ እንደ አለቃ ጥበቡ፣ አለቃ ደስታ ነገም፣ መሪጌታ ወልዴ እና መሪጌታ ከበደን የመሳሰሉ ኦሮሞዎች እንዳሉ የማያውቅ ወይም ለማወቅ የማይፈልግ ምን ዓይነቱ ጂል ነው!

በርግጥ ያን ያህል ያብከነከነው ችግረኛውን አማራ ደግፌ የጻፍኩት ግጥም ነው፡፡ ነቃፊዬ አማራ ወይም ኦሮሞ እንዳልሆነ ግልጽ ነበር፡፡ ምክንያቱም አንዳቸውም ራሳቸውን የሚሰድቡና ስለ አንድነት የተጻፈን ግጥም የሚቃወሙ አይደሉምና፡፡ ከደቡብ ኢትዮጵያ እንዳልሆነም ተረድቻለሁ፡፡ ከየት ሊሆን እንደሚችል አንባቢዬ እንደሚገምተው እኔም እገምታለሁ፡፡ መለስ ብዬ ሳስበው አንድ ነገር ላይ ርግጠኛ ነኝ፡፡ የዘር ጥላቻ የሚያስራጭ፣ የኢትዮጵያ ጠላት የሆነ፣ ከሰው ተራ የወረደ፣ ያልሰለጠነ፣ ኋላቀር ከፉ እውሬ ነው፡፡ እሱን መልሶ መስደብ ዓየር የመሳብ ያህል ቀላል ነበር፡፡ ሆኖም እንደዚያ ማድረግ እንደሱ ዝቅ ማለት በመሆኑ ትቼዋለሁ፡፡ ከሱ ጋር መመላለስ ክብር እንዲስማው ማድረግ መስሎ ተሰማኝ፡፡ ስለዚህ በዚች ዓለም ላይ ያልተፈጠረ ያህል ንቄ ተውኩት፡፡ እሱ ግን እንድናደድና የሱን ዘር በሙሉ በግምት እንድጠላ ተንኩሶኝ ነበር፡፡ ያ ደግሞ ኢ-ምክንያታዊነት ነው ለኔ፡፡ በሱ የተነሳ ከኢትዮጵያ ለንደቅዐላማ፣ ከባሕሏም ጋር ምንም ጉዳይ የለኝም ብዬ ኢትዮጵያዊነቴን አልክድም፡፡ በፍጹም ይህን አላደርገውም፡፡ በዚያ ሁኔታ ላይ የተማረሩ ወንድሞቼ እና እህቶቼ ምን እንደሚሰማቸው የበለጠ እረዳለሁ እንጂ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በየትኛውም ቦታ ያጋጥሟቸው በነበሩ ይህን በመሳሰሉ የወረዱ እንስሶች በጣም ይበሳጩ የነበሩ የኦሮሞ ወገኖቼ አሉ፡፡ ለነዚህ ወገኖቼ የምሰግስው ምክር በእንደዚህ ዓይነቱ እርጉም አውሬ የተነከል ድርጊት እንዳይናደዱ ነው፡፡ ማን መሆናችሁን ታውቃላችሁ፡፡ የነገሥታት ንጉሥ፣ የካህናት አለቃ እና የሁሉም ኢትዮጵያውያን እባት የነበረው

የኢትዮጵ፣ እንዲሁም ሙት ታስነሳ የነበረችውና የደሽት ወላጅ እናት የሆነችው የታሳቅዋ ነቢይት የሽምሽል እና የነቢዩና የጠቢቡ የደሽት የራሱ ተወላጆች ናችሁ። እንዲሁም የኦሮሞ እና የአማራ ምንጭ የሆነው የታላቁ ፈላስፋ እና ነቢይ የደሽት ልጆች ናችሁ። ምንጫችንን ይበልጥ ራቅ ስናደርገው ደግሞ አይሁዶች ገና ወደ አካባቢው ከመምጣታቸው በፊት የኢየሩሳሌም ገንቢ እና ንጉሥ የነበረው ከሃሊውን ግዚአብሄርን በምድር ላይ የወከለው፥ የካህናቶች ካህናት፥ የንጉሦች ንጉሥ የመልከፃዲቅ ዝርያ ነን። ለዚህ ለትልቁ አባታችን የአይሁዶች አባት የሆነው አብርሃም ታሳቅነቱን አክብሮ ይሰግድለት እና ምርቃቱን ለማግኘት አሥራት ያገባለት ነበር። ይህንንም አባታችንን፥ እንዲሁም ኢትዮጵን እና ደሽትን፥ አማሮችና ሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ዘመዶቻችን ከኛ ጋራ ይጋሩአቸዋል።

ኢትዮጵያን ለምን በጣም እንደማፈቅራት እና ኢትዮጵያዊነቴንም ለምን እንደምወድ አንዳንድ ኦሮሞ ወዳጆቼ ይገርማቸዋል። ኢትዮጵያን አፈቅራታለሁ፤ ምክንያቱም የኦሮሞ እና የሁሉም ኢትዮጵያውያን መገኛ የሆነውን የታላቁን አባታችንን የኢትዮጵን ስም ይዛለች። ኢትዮጵያዊነቴንም እወደዋለሁ፤ ምክንያቱም አያት ቅድመ-አያቶቼ በዓለም መድረክ ላይ የተጫወቱት ሚና ያኮራኛል። አያት ቅድመ-አያቶቼ ልዩ የሆነውን ቅርሳቸውን የተውልን የኢትዮጵያን ዳር ድንበር አዘልለው መሆኑን አውቃለሁ። ስለዚህ ራሴን "ኦሮምያ" በምትባል ጠባብ ቦታ ላይ ብቻ መወሰን አልፈልግም። ምክንያቱም ጠቅላላዋ ኢትዮጵያ በመላው ቁመትዋ እና ስፋትዋ የኔ፣ የኦሮሞ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ እንዲሁም የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ናት። እሰዋንም ለማትረፍ እና ለኛ ለማስተላለፍ ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስክሰዋልና። በሕዝቦቿ ቅርፀ-መልክ፣ በቋንቋዎቿ ብርቅነት፣ በሙዚቃዋ ጥልቀት፣ በጭፈራዋ አማላይነት፣ በስነ-ቃልዋ፣ በታሪኳ፣ በፍልስፍናዋ እና በስነ-ጽሑፍዋ እማረካለሁ። በቤተክርስቲያን ስነ-ሥርዓትዋ እና በሃይማኖትዋ፣ በዜጎቿ መልካም ጠባይ፣ በጨዋነታቸው፣ ለሕይወት ባላቸው አመለካከት እና በአእምሮአቸው ረቂቅነት እና ጥልቀት እሳባለሁ። በክብራቸው አስፈሪነት፣ በንግግራቸው ተራቃቂነት፣ በጥበባቸው ውስብስብነት፣ ከችግራቸው ባሻገር በአለው ኩራታቸው ጥልቀት እና ተወዳዳሪ በማይገኝለት ገርነታቸው እና በተቅለመለመው ብዙሐንነታቸው እሸነፋለሁ። የኦሮሞዎችን እና የአማሮችን ጨምሮ ይህን እና ይህን

መሳዩ የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን ባህርይ እና ማንነት ለኢትዮጵያ እና ለልጆቿ ስሜታዊ እንድሆን ያስገድዱኛል።

ስለዚህ እኔ ፍቅሬ ቶሎሳ (ቶለሳ) ጂግሳ፣ የሳሌም ንጉሥ እና የእግዚአብሔር ከፍተኛ ካህን የነበረው የመልከጼዴቅ ልጅ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት እና የዐለማቱ ፈጣሪ ከፍተኛ ካህን የነበረው የኢትዮጵ ልጅ፣ እንዲሁም ነቢይ እና ፈላስፋ የነበረው የጎጃም ንጉሥ የደሸት ልጅ ነኝ። አዎ! ኦሮሞዎችን፣ አማሮችን፣ ሃድያዎችን፣ ከምባታዎችን፣ ሶማሊዎችን አፋሮችን፣ ጉራጌዎችን እና ሌሎቹንም ኢትዮጵያውን ጨምሮ እንደ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ እኔም የነዚህ ሁሉ ልጅ ነኝ።

የኢትዮጵ ልጆች መሆን እና በዚህም ኢትዮጵያዊ መሆን የሚታፈርበት ሳይሆን የሚኩራበት ነው። የመልከጼዴቅ እና የኢትዮጵ ተወላጅ መሆን የሚያስገርም እና በእጅጉ የሚያኩራ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው እየሱስ ክርስቶስ ወደፊት በኢየሩሳሌም በሚገዛበት ወቅት በመልከጼዴቅ ሥርዓት መሰረት ነው የሚገዛው። (53) በርግጥ የሚታየውን እና የማይታዩትን ዐለማት የፈጠረ እየሱስ ክርስቶስ የሙሴ ወንድም እና የአይሁድ ከፍተኛ ካህን በነበረው በአሮን ስርዐት አይደለም የሚገዛው። የአሮን ካህንነት ከመልከጼዴቅ እና ከኢትዮጵ እጅግ ዝቅ ያለ ነው። እንዲሁም የንግሥተ-ሳባ እና የንጉሥ ሰለሞን ልጅ እስከ ሆነውና ከእናቱ ሃይማኖትና ባሕል ይልቅ የአባቱ ሃይማኖትና ባሕል በልጣበት ሊቀ-ካህናትነትን በአይሁድነት እለከለወጠው እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ ድረስ ለአንድ ሺ አመታት ባንድ ጊዜ የነገሥታት ንጉሦች እና የካህናት አለቆች ከነበሩት ስፍር ቁጥር ከሌላቸው ከኢትዮጵ ወራሾች ካህንነት በጣም ያነሰ ነው።

ልድገመውና የመልከጼዴቅ፣ የኢትዮጵ እና የተከታዮቹ ንጉሠ-ነገሥትነት እና ሊቀ-ካህናትነት ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ልንኩራበት የሚገባን ትልቅ ነገር ነው።

የኢትዮጵ ልጆች በመሆናችንም ልንኩራ ይገባናል፤ ምክንያቱም ከ4000 ዓመት በፊት የኢትዮጵያን ግዛት መሰርቶልናል፤ መጻህፍትም ጽፏል፤ ስለ መንግሥት መዋቅር እና ስለ ህገ-መንግሥት ተከታዮቹን አስተምሯል፤ ፊደላችንን አሻሽሏል።(54) ባለፉት ጊዜያት መላው

አፍሪቃ ኢትዮጵያ እየተባለ እንዲጠራ ምክንያት ሆኗል፤ እንዲሁም ታላቅነቱንና ምርቃቱን ለልጆቹ አስተላልፎ ነገሥታት፤ ከፍተኛ ካህናት፣ ነቢያት፣ ፈርኦኖች እና ህንደኬዎች እየሆኑ ኢትዮጵያን፣ እስያን፣ አረቢያን፣ ኒጀርን፣ ናይጀሪያን፣ ግብፅን፣ ኑቢያን፣ ሱዳንን፣ ታንዛኒያን፣ ሞሪታኒያን እና ሊቢያን በጽድቅና በፍትህ አስተዳድረዋል። የኢትዮጵያን ሥልጣኔንም አስራጭተዋል፡፡ ከታላላቅ ንግሥታት መካከል ፋሲላ እኖኒ በሚል ስያሜ የምትጠራውና በአጼ ፈንታሌ ተሾማ 13ኛዋ ህንደኬ የነበረችው መደባይዋ ኦሮሞ ትጠቀሳለች፡፡(55)

ቀደም ሲል እንደዘረዘርኩት ከ2000 አመታት በኋላ አጼ ባዚን ንጉሠ-ነገሥት በነበረበት ወቅት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "የምሥራቅ ጠቢባን" የተባሉት 12ቱ የኢትዮጵ ዝርያዎች አሥራ ሁለት ነገሥታት እና ጠቢባን ሆነዋል፡፡ እጆቻቸውን ለእግዚአብሔር ዘርግተውም "ዮጽ" በመባል የሚታወቀውን ልዩዉን የኢትዮጵያን ቢጫ ወርቅ፣ ከርቤ እና እጣን ሥጦታ አበርክተዋል፡፡ የእየሱስ የሥጋ ዘመዶች የሆኑት አይሁዳዉያን መወለዱን እንኳ ገና ሳይሰሙ ነው እንግዲህ በትንቢቱ መሰረት እነዚህ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ትንቢቱን የፈፀሙት፡፡ ትንቢቱም "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የሚለው ነው(56)፡፡ እነዚህ አሥራ ሁለት "ወንድማማች ንጉሦች" ሁሉንም የኢትዮጵያን ሕዝቦች ይወክላሉ፡፡ ለምሳሌ ንጉሥ መጋል፣ ንጉሥ ሙርኖ፣ ንጉሥ መቃዲሺ እና ንጉሥ አጎጃ ጀባን እንደ ቅደም ተከተላቸው ኦሮሞን፣ አፋርን፣ ሶማሌን አና አማራን ይወክላሉ፡፡

ከ3500 ዓመት በፊት ሌላው የኢትዮጵ ተወላጅ የሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምድያም ሊቀ ካህናት እና የሙሴ አማት፣ እኛ ኢትዮጵያውያን የትሮ-አብ ብለን የምንጠራው ትልቅ ሰው ነው፡፡ ሙሴን በእግዚአብሔር ሥርዓት ለ40 ዓመት ያሰለጠነው፡፡ ከዚህም በላይ፥ በአይሁዳውያን መካከል ይነሳ የነበረውን ፀብና ውዝግብ ሙሴ ለብቻው ለመዳኘት ሲደክምና አይሁዳውያኑም ሲጉላሉ ዐይቶ ሙሴ የፍትህ እና የፍርድ ሥርዓት እንዴት መዘርጋት እንደ አለበት የመከረው እሱው ነው፡፡ (56)

እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ነጻ ለማውጣት የተጠቀመበት እና ቃል በቃል በቀጥታ እያነጋገረው አሥርቱ

ትዕዛዛትን የሰጠው ብቸኛው ሰው ሙሴ በመሆኑ ሙሴ እንደ ታላቅ ሰው ይታይ ነበር። የኛ የኢትዮጵያውያን ጥንተ-አባት የትሮአብ ግን ከሙሴ እጅግ የሚልቅ ታላቅ ሰው ነበር። ምክንያቱም ቃለ-እግዚአብሄርን፣ መንገደ መለኮትን እና የፍትህ ሥርዓት አዘረጋግን ለሙሴ ያስተማረ የታላቁ እግዚአብሔር ሊቀ ካህን ነበርና። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተገለጸው ሙሴ ለየትሮአብ ባክብሮት ቢያነነብስለት አያስገርምም። የትሮአብ የመልከፀዴቅ እና የኢትዮጵ ዝርያ ስለነበረ እሥራኤላውን ከባርነት ነፃ ከወጡ ከ3 ዓመታት በሑዋላ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሆነ። አይሁዶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሃባብ ብለው የሚጠሩት የየትሮአብ ልጅ አባ-ብሄር በታላቁ ካህን ልጅነቱ ቃለ-እግዚአብሄርን በደንብ ያውቅ ስለነበር በጉዞአቸው ላይ ህዝቡን በማስተማር ረገድ ሙሴን ለብዙ አመታት ረድቶታል። (57)

የጥንተ-አባታችን የኢትዮጵ ዝርያ ከሆኑ ታላላቅ እንስቶች መካከል፤ የንጉሥ ሰለሞንን ጥበበ-እውቀት ሽታ ከኢትዮጵያ ኢየሩሳሌም ድረስ በመጓዝዋ እየሱስ ያሞገሳት ኤትያኤል (ንግሥተ-ሳባ) (58)፣ በዘራቸው ኢትዮጲያውያን የነበሩት የንጉሥ ዳዊት አያት ሩት እና ሐብሴ እያልን የምንጠራት ወላጅ እናቱ አዶሲያ ይጠቀሳሉ። ሩት ዓለምን የሚያድነውን ኮከብ (የእየሱስን) መወለድ የተነበየው የነቢዩ በልአም የልጅ ልጅ ስትሆን እርሷ ራሷም ስለ ኮከቡ መወለድ ራዕይ ዐይታ ስለ ነበር ያየችውን ራዕይ ለማሰብ የኮከቡን ቅርፅ ስርታ በልጅዋ በአቤድ አንገት ላይ አስራላት ነበር። ውሎ አድሮ ንጉሥ ዳዊት ያንን የኮከብ የእጅ-ሥራ ከእናቱ ወረሰ። ዛሬ ድረስ የአይሁድ ሕዝቦች እና መላው ዓለም ያንን የኮከብ ቅርፅ "የዳዊት ኮከብ" እያሉ ይጠሩታል። ስለ ኮከቡ ሠራተኛ ስለ ሩት ግን ምንም አይነሳም። እየሱስ ክርስቶስ "የዳዊት ልጅ" እየተባለ ስለሚጠራ እና እናቱ የኛዋ ኢትጵያዊትዋ አዶሲያ (ሐብሴ) በመሆንዋ(59) በእየሱስ ክርስቶስ ደም ውስጥ ኢትዮጵያዊ ደም ስላለ እየሱስ ክርስቶስ የስጋ ዘመዳችን ነው ብንል ያስኬዳል። ታዲያ ይህ ሁሉ በኢትጵያውነታችን የሚያኮራን አይደለምን?

የስንደቅ ዓላማን ጉዳይ በተመለከተ ከኦሮሞ የነፃነት ተዋጊዎች ጋር የተያያዘ ስንደቅ ዓላማ አለ። አራት ወይም ሶስት የተለያዩ ሰንደቅ ዓላማዎች ነበሯቸው። በቀይ እና በአረንጓዴ ቀለማት ያጌጠውንና ማሕሉ ላይ ዋርካ ዛፍ ያለበትን እመርጠዋለሁ። ምክንያቱም የኦሮሞ

አዛውንት አካባቢያቸውን እና ሕይወታቸውን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለመምከር ሲሰበሰቡ ከሚጠለሉባቸው ዛፎች አንዱ የተወከለበት ስለሆነ ነው። ባለፈው ጊዜ ስለነበረው የኦሮሞ ዴሞክራሲ ብዙ የሚናገረው አለ። አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለማት ያሏትን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማም እወዳታለሁ። እስዋንም የምወድበት በቂ ምክንያት አለኝ፤ ከ3400 ዓመት በፊት የፈጠራት የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የአፋር፣ የሶማሊ፣ የሀዲያ እና የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት የሆነውና በንግሥና ስሙ "ሰንደቅ አልማ" ይባል የነበረው እጌ ወይም እሴ በመሆኑ ነው።(60) ሰንደቅ-ዐላማ የተባለችው ለዚህ ነው። እሴ የኢትዮጵ ዝርያ ሲሆን እኔ እስከማውቀው ድረስ ፍፁም አቻ የሌለው እጅግ ታላቅ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ነበር። በመልከጼዴቅ እና በኢትዮጵ ስርዐት መሰረት መንፈሳዊውንና ዓለማዊውን ሥልጣናት አጣምሮ የያዘ ሊቀ-ካህናት እና ንጉሠ-ነገሥት ነበር። እንደ አባቶቹ እሱም ሁለት ታላላቅ ሥልጣኖች ነበሩት ማለት ነው፡- መንፈሳዊ እና ፖለቲካዊ። ከፍ ያለ ዝናን ያተረፈ፣ እንደ ጥንታዉያን የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች የረጂም ዕድሜ ባለፀጋነትን ምስጢር ተረድቶ 480 ዓመት የኖረ፣ ሩቅ ምሥራቅን አስገብሮ በክህነት ስሙ "እስያ" ብሎ ሰይሞ(61) እስከ ዛሬ አህጉሩ "እስያ" እየተባለ የሚጠራለት እጅግ ታላቅ ንጉሠ-ነገሥት ነበር።

እሴ ልዩ ችሎታ የነበረው ሳይንቲስትም ነበር። አዝዕርትንና እፅዋትን እንዲሁም እንስሳትን እያዳቀለና አዳዲስ እፅዋትንና የእንስሳት ዝርያዎችን እያስገኘ በቤተ-መንግሥቱ ያኖር የነበረ የመጀመሪያው በራሄ-ጂን/ዘረ-መል/ መሐንዲስ (Genetic Engineer) ነበር። በሰው በራሄ-ጅን DNA ላይም ምርምር ያደርግ ስለ ነበር ኢትዮጵያውያንን ከእስያውያን፣ እና ከመካከለኛው ምሥራቅ ምርኮኞቹ ጋር እያጋባ ዛሬ ያለን ልዩ የሆነው ቅይጥይጥ የቆዳ ቀለም፣ የፊት ቅርጽ፥ የተለያየ የጸጉር አሠራር እና ልዩ ልዩ የነገድ አካላዊ ቅርፀ-መልክ እንዲኖረን አስችሏል። የተለያዩ ቀለማት እንዳሉት ውብ አበባ በልዩነት እንድናምር ያደረገን እሱ ነው። የቋጥኞችን ተፈጥሮ የተረዳ ጂኦሎጂስት እና አንዳንድ እንስሳትን ከሌሎች ጋር እያዳቀለ አዳዲስ እንስሳት እንዲፈጠሩ ያደረገ ታላቅ ሳይንቲስትም ነበር። በፈልሳፊነቱም ገና በጥንቱ ዘመን የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዐላማ ፈጥሮ የመንግሥት ባለሥልጣናት በየሥራ ቦታዎቻቸውና በየ ሰረገላዎቻቸው ላይ

እንዲሁም ከስራዊቶቻቸው ፊት እና ኋላ እንዲያውለበልቧት በሕግ ደንግጓል። ይህን ሲያደርግ ምናልባት በዐለም የመጀመሪያው መሪ ሳይሆን አይቀርም። የሰንደቅ ዓላማው ቀለም አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ሰማያዊ ነበር። በጥቁር አባይ መነሻ ላይ ሆኖ የሰንደቅ-ዐላማዋን መፈጠር ባወጀበት ዕለት ለዜጎቹ ንግግር ሲያደርግ እግዚአብሔር ምድርን ዳግመኛ በውሀ እንደማያጠፋት ለኖኅ ቃል እንደገባለት እና ለቃል ኪዳኑ ምልክት ቀስተ-ዳመናን እንዳቆመ፤ የቀስተ-ደመናው ቀለማትም የአግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንደሚወክሉ አስታውሶ በተመሳሳይ መንገድ አጼም በነገሥታት እና በሕዝቦች፣ በሱ እና በተወዳጅ ዜጎቹ መካከል ያለውን ፍቅር ለማሰብ ሰንደቅ-ዐላማዋ ከፍ ብላ እንደምትውለበለብ ማድረጉን ገልጾ ነበር። በገለጸው መሰረት አረንጓዴ ምድራዊነትን፣ ቢጫ ፍቅራችንን፣ ሰማያዊ ደግሞ መንፈሳዊነታችንን ይወክላሉ። የመስቀያው አናት በወርቅ እና በብር የተሰበጠ የኮከብ ቅርፅ እንዲሆንና ሰንደቅ-ዐላማዋን ያላውለበለበ ማንኛውም ባለሥልጣን በጥብቅ እንዲቀጣ ደንግጎ ነበር።(62)

እንግዲህ ሰንደቅ-ዐላማችን በአጼ አስያኤል ለመፈጠርዋና የ3300 ዓመት እድሜ ባለጸጋ ለመሆንዋ ማስረጃው አጼ በዚህ ዘመን መግዛቱ የተመዘገበ መሆኑ እና "ሰንደቅ-ዐልማ" ስመ-መንግሥቱ እንደነበረ መረጋገጡ እንዲሁም ሰንደቅ-ዐላማችን የዚያን ልዕለ-ሰብ መሪ ስም ይዛ እስከዛሬ "ሰንደቅ-ዐላማ" እየተባለች መጠራትዋ ነው። ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ከውጪ ወራሪዎች ሲከላከሉ ያፈሰሱትን እና የሚያፈሱትን ደም ለመወከል ታስቦ ከጊዜ በኋላ ሰማያዊው በቀይ ተተክቷል። ከ700 ዓመታት በፊት ይኩኖ አምላክ (የኦሮሞው ዝርያ ንጉሠ-ነገሥት) እና ነአኩቶ ለአብ (የዛጉዌው ንጉሠ-ነገሥት) በአቡነ ተክለሃይማኖት ሽምጋይነት የዛጉዌን ሥርወ-መንግሥት ለሠለሞን ሥርወ-መንግሥት አባላት ለማስተላለፍ ሲስማሙ ይቺ ሰንደቅ-ዐላማ እንደገና ተጠቅሳለች። (63)

አዎ! በርካታ ኦሮሞዎች፣ አማሮች፣ አፋሮች፣ ሀዲያዎች፣ ትግሬዎች እና ሌሎችም ኢትዮጵያውን ይቺ ሰንደቅ-ዐላማ በነፃነት አየር ላይ በክብር እንድትውለበለብ ደማቸውን አፍሰስዋል። ከ24 ዓመት በፊት አንዱ ከእሷ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ግለሰብ ባርቆበት እንደነበረው ላባቶቻችን ይቺ ሰንደቅ-ዐላማ ተራ "ጨርቅ" አይደለችም። የሚገርመው ያ ግለሰብ ሞቶ ወደ መቃብር ሲወርድ

አስክሬኑ ይቺኑ የጠላትንና "ጨርቅ" ብሎ ያናናቃትን ሰንደቅ-ዐላማ ለብሶ መታየቱ ነው።

በቅርቡ ያገራችን ታሪክ በአድዋ፥ በማይጨውና በደፈጣ ውጊያ ጦርነቶች እንኳዋ ለዚች ሰንደቅ-ዐላማ ከተፋለሙ ኦሮሞዎች ጥቂቶቹን ለማስታወስ፣ የአጼ ምኒልክ ባለቤት ንግሥት ጣይቱ ብጡል፣ ፊታውራሪ ሃብተ-ጊዮርጊስ ዲነግዴ፣ ፊታውራሪ ባልቻ አባ-ነፍሶ፣ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ ጄኔራል ጃጋማ ኬሎ፣ እና ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ፣ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ፣ ኮሎኔል አብዲሳ አጋ፣ ራስ አበበ አረጋይ፣ ደጃዝማች ገብረ-ማሪያም ጋሪ እና ወይዘሮ ልክ የለሽ በያን የሚጠቀሱ ናቸው። የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዐላማ በነጻነት ዓየር ላይ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ በጀግንነት የተዋጉትንና ያልተዘመረላቸውን የኦሮሞ ጦረኞች በሙሉ እዚህ መዘርዘር ያስቸግራል።

አባቴ ቶሎሳ(ቶለሳ) ጂግሳ ዋኬኔ ሰላማዊ ዜጋ እንጂ ጦረኛ አልነበሩም። ዳሩ ግን የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዐላማ በኢትዮጵያ ዐየር ላይ ለማውለብለብ ከጣልያን መፋለም ነበረባቸው። በወለጋው ገዢ በቢትወደድ መኮንን ደምሴ ስር ሆነው በ1928 ዓ.ም በማይጨው ጦርነት ከፋሺስት ጣልያን ጋር ተዋግተዋል። የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዐላማ ለኢትዮጵያውያን የነጻነት ምልክት ነበረች፤ ነችም። በኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዐላማ ቀለማት የተሠራ ያንገት ልብስ አንገቴ ላይ ጣል አድርጌ ያየኝ አንድ ወጣት ኦሮሞ ባንድ ወቅት አንባረቀብኝ። ሰንደቅ-ዐላማዋ ከ3300 ዓመታት በፊት በራሱ ቅድመ አያት የተፈለሰፈች እና በርካታ አባቶቹ እና እናቶቹ ለህልውናዋ የተዋደቁላት መሆንዋን ቢያውቅ ኖሮ ይህን ያህል ጠላትዋ አይሆንም ነበር። በቅርቡም አረብ አገር በሠራተኛነት የምታገለግል አንዲት ኦሮሞ ሴት የኢትዮጵያን ባንዲራ በጥላቻ አቃጥላለች። ጥንተ-አባትዋ አጼ ወይም እሴ እና ለሰንደቅ-ዐላማዋ ሕልውና የተዋደቁ እነዚያ ሁሉ ታላላቅ ኦሮሞዎች ድርጊትዋን ቢያዩ ኖሮ በመቃብር ውስጥ አጽማቸው በሀዘን በተገላበጠ ነበር።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዐላማ በሌሎች እልፍ አእላፍ ኢትዮጵያውን ግን እጅግ ትፈቀራለች። ለምሳሌ አርቀ አሳቢው የአፋሮች መሪ ክቡር ደጃዝማች ዓሊ ሚራህ ባንድ ወቅት "እኛ ቀርተን ግመሎቻችን እንኳዋ የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዐላማ ያውቋታል" ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያውያንን በሙሉ የሚወክል ብሔራዊ ምልክት መኖር ስላለበት ሁሉም ኢትዮጵውያን ይቺን ሰንደቅ-ዐላማ ከፍ እድርገው ማውለብለብ ይገባቸዋል። ይህ ሀቅ የተለያዩ ጎሳዎች ልዩ የሆነውን ቅርሳቸውን እና ባሕላቸውን የሚያንጸባርቅ የራሳቸው የጎሳ አርማ እንዳይኖራቸው የሚያግድ አይደለም። ለምሳሌ የኦሮሞ ነጻነት ተፋላሚዎች መካከሉ ላይ የዋርካ ዛፍ ያለበት አርማ እላቸው። ይህንን አርማ ካገራቸው ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዐላማ ጋር በየአካባቢያቸው ከፍ አድርገው ማውለብለብ ይችላሉ። ይሁንና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምልክት የሆነችው ሰንደቅ-ዐላማ ከሁሉም አካባቢያዊ እርማዎች ቀድማ መውጣት፣ ልቃ መታየት አለባት። ምክንያቱም የሁላችንም የሆነችዋን አንዲት አገር የምትወክል የአንድነት ተምሳሌት ናትና። አንድ ቡድን በሌሎች ጎሣዎች ላይ የራሱን እርማ ብቻ ልጫንባችሁ ቢል ኢ-ፍትሀዊነት እና ጭቆና ነው። እርማው በማይወክላቸው ጎሳዎች ላይ፣ ለምሳሌ ሠንደቅ-ዐላማችንን "ግመሎቻችን እንኳ ያውቋታል" በሚሉት በአፋሮች ላይ ብሄራዊው ሰንደቅ-ዐላማ ቀርቶ ያንድ ጎሳ አርማ ብቻ ይውለብለብባችሁ ማለት እግባብ አይደለም። አሁን የእለችው ባለ አረንጓዴ፥ ቢጫ፥ ቀይ ቀለም ሰንደቅ-ዐላማ ለበርካታዎቹ ኢትዮጵያውያን ጥልቅ ትርጉም አላት። ትርጉሙ ከአሮሞዎችም ጋር ይያያዛል። እረንጓዴው የኢትዮጵያን ልምላሜ ብቻ ሳይሆን የኦሮሞንም ምድር እረንጓዴነት ያመላክታል። ኦሮሞዎች የሚወዱአቸውን ጨፌዎች እና ዛፎችን ጭምር። ቢጫው መንፈሳዊነትን ሲገልፅ፥ የጥንቶቹን ከኢትዮጵና ከደሸት በቀጥታ የወረዱትን የአሮሞ ነቢያት እና ካህናት መንፈሳዊነትንም ጭምር ያንፀባርቃል። ቀዩ ደግሞ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከውጪ ወራሪዎች ለመከላከል፥ ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር ሆነው ኦሮሞዎች ያፈሰሱትን ደም ይዘክራል። ስለዚህ ስስቱም ቀለማትና ሰንደቅ-ዐላማዋ ራስዋ ከአሮሞዎች ጋር የቀጥታ ግንኙነት አላቸው። የጎሣ አርማንና የሀገር ሰንደቅእላማን አስመልክቶ የምለው ይህንኑ ነው።

የሀረሩ እውሳ አዳል ግራእጁ አህመድ ኢብራሂም መሀመድ ምንም እንኳን መፃህፍትና አብያተክርትያን ቢያቃጥልም፥ የሚመሰገንበት ገድል ነበረው። ከሁሉ አስቀድሞ በኢትዮጵያዊነቱ፥ በኢትዮጵያ ሰንደቅአላማና በኢትዮጵያ አንድነት እይደራደርም ነበር። ቱርኮችና እረቦች ኢትዮጵያን እንዲያጠፋ ሊጠቀሙበት የጦርመሳሪያና

የራሳቸውን ወታደሮች ቢሰጡትም፥ ሙሉ በሙሉ አሸንጉሊታቸው ሆኖ ፍላጎታቸውን አላሙዋላላቸውም። አብረውት የነበሩት ሱማሌዎች የእኛ ግዛት ከአዋሽ ማዶ አይደለም ሲሉት፥ ቱርኮቹም ያንተ ግዛት ከአዋሽ በታች ነውና ከዛ አትለፍ ተመለስ ሲሉት፥ የእሱ እቅድ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ መግዛት ብቻ ሳይሆን የጥንትዋን ኢትዮጵያን ክብርና ዝና ለማስመለስ ግብፅ'ኑ የመንን እና ሱዳንን ጭምር ለመቆጣጠር ስለነበር አሻፈረኝ አላቸው። ሱማሌዎቹንም ፈጃቸው።

አላይ በተጠቀሰው ምክንያት በተሰለፈበት ቦታ ሁሉ የኢትዮጵያን አረንጓዴ፥ ቢጫ ቀይ ሰንደቅአላማ እና አረቦች የቸሩትን የእስልምና ሃይማኖቱን የሚወክለውን ግማሽ ጨረቃ ያለበትን አረንጓዴ አርማ በኩራት ያውለበልብ ነበር። የሁዋላ ሁዋላ መላውን ኢትዮጵያን አጠቃልላለሁ ቢልም በመጀመሪያ አነሳሱ ከንጉሠነገሥቱ፥ ከኦሮሞው ተወላጅ ከአፄ ልብነድንግል እውቅና አግኝቶ የንጉሡን ሴት ልጅ አምራ-ፅዮንን አግብቶ ከአዋሽ መለስ እስከ ሀረር ለመግዛት ነበር ። ስለዚህም ንጉሡን፥ ልጅህን አምራ-ፅዮንን ዳርልኝና አስልሜ አግብቻት፥ ተዛምደን ከአዋሽ በታች እየገዛሁ ግብሬን እያገባሁልህ ላገልግልህ፤ ፍቅራችንም ይፅና፤ ብሎ ደብዳቤ ጻፈለት። ክርስትያኑ ንጉሥ ግን አልባሌ ነው ብሎ የሚያስበውና ክርስትያን ያልሆነው ሰው ልጅህን ላግባ በማለቱ እንደ ድፍረት ቆጥሮት የዛቻ ደብዳቤ መለሰለት። ግራኟ አህመድም በዚህ ተናዶ ጦርነቱን ቀጥሎ ንጉሡን እና ቤተሰቡን እስከመጨረሻው አሳደዳቸው። ልእልት አምራ-ፅዮንም እንኳን ልታገባው ቀርቶ፥ ግራኝን በጀግንነት ተዋግታው ሞተች።

ግራኝ አህመድ ግን ያን ሁሉ ጦርነት ያኪያሂድ የነበረው በሙስሊም ሰራዊት ብቻ ታጅቦ አልነበረም። ከሙስሊሞቹ ጋር የተደባለቁ የአማራ ክርስትያን፥ የኦሮሞና የሌሎችም ጎሳዎች ሰሙ ይዋጉለት ነበር። በማእረጋቸውም እስከ ደጃዝማች ያደርሳቸው ነበር። ቢሆንለት ኖሮ የእስላም መንግሥት መስርቶ፥ ሃበሻ ያላትን መላዋን ኢትዮጵያን በስነስርአት ለማስተዳደር ያስብ ነበር እንጂ ቅዋሜ ያላኪያሄዱበትን ዜጎቹን ወይም በግዛቱ ስር የወደቁቱን ወገኖቹን የግድ ስለሙ ብሎ አያስጨንቅም ነበር። እኔን ካልተቃወማችሁኝ በመሬታችሁና በሃይማኖታችሁ እንድትፀኑ እፈቅድላችሁአለሁ።

ከተቃወማችሁኝ ግን፥ማስለም ብቻ አይደለም ባርያ አድርጌ ለአረቦች አሸጣችሁአለሁ ብሎ አውጆ ነበር። ያለውንም አድርጎታል።

እንግሊዞች በአፄ ቴዎድሮስ ላይ ላደረጉት የመጨረሻ ውድቀት ተጠያቂ አፄ ዮሃንስን ብቻ የሚያደርጉ ሰዎች አሉ። ስለ እውነት እንነጋገር ከተባለ፥ እሳቸው ብቻ ተጠያቂ አይሆኑም። እሳቸው በአፄ ቴዎድሮስ ላይ የነበራቸው የግል ቂም ብቻ ነው። እሱም እንደኛ፥ እሳቸው ካሳ ምርጫ ተብለው በሚጠሩበት ሰዐት የአፄ ቴዎድሮስ ወታደር ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተው አምባቦ ላይ ከደጃዝማች ውቤ ጋር አፄ ቴዎድሮስ ሲዋጉ፥ ካሳ ምርጫና የእናታቸው ወንድም አጎታቸው አርአያ ድምፁ ተሳትፈው ነበር። አርአያ ድምፁ ከደጃዝማች ውቤ ተጣልተው፥ ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር አድመው፥ በዚሁ በአንባቦ ጦርነት ላይ ጀብድ በመሥራታቸው ከድል በሁዋላ ራስ ብለው ሾመው የትግራይ ገዢ አደረጉዋቸው። ካሳ ምርጫ ግን ምንም ልዩ ጀብድ ባለማሳየታቸው ባላምባራስ ብለው የመጨረሻ ዝቅተኛ ማእረግ ዳረጉዋቸው። ይህ ካሳ ምርጫን አስቆጣቸው። በሞግዜአቸው በካሳ ኃይሉ ላይ ቂም እንዲይዙም አስገደዳቸው። ይህ በእንደዚህ እያለ አፄ ቴዎድሮስ ሸዋን በወረሩበት ሰዐት በሰላም የተቀበለንን አትዝረፉ ብለው ለወታደሮቻቸው አወጁ። የባላምባራስ ካሳ ምርጫ ሰራዊት ግን አዋጁን ጥሶ ከመንደር ገብቶ ሲዘርፍ ባላገሩ የአፄ ቴዎድሮስን ትእዛዝ ሰምቶ ስለነበር ዘራፊዎቹን ተቃውሞ አሳደዳቸው። ዘራፊዎቹ ሲሮጡ ያዩት አፄ ቴዎድሮስ የሚሮጡበት ምክንትያት ሲነገራቸው ሲሆን አዋጁን አክብረው ባላገሩን አለመዝረፍ ነበረባቸው። ከዘረፉ ደግሞ ቆመው መጋተር ነበረባቸው እንጂ ወታደሮች ሆነው እንዴት ይሸሻሉ፥ ብለው በንዴት እጅ እግራቸውን ቆረጡአቸው። በላምባራስ ካሳ በዚህ ተበሳጭተውና ይበልጥ ቂም ይዘው ወደ ሀውዜን ሄደው አገው ንጉሴ ከተባለ አንድ እልህ አስጨራሽ የአፄ ቴዋድሮስ ጠላት ጋር አብረው ሸፈቱ። ከዛም ከእንግሊዞችና ፈረንሳይዎች ጋር ደብዳቤ እየተላላኩ በንጉሠነገሥቱ ላይ እያሴሩና እርዳታ እየጠየቁ ከረሙ። እንግሊዞች አፄ ቴዎድሮስን ሊቀጡ በመጡ ጊዜ ባላምባራስ በአጋጣሚው ተጠቅመው ከእንግሊዞች ተመሳጠሩ። ይሄው ነው። ይህንንም ተንኮል ባላምበራሱ ብቻ ሳይሆኑ በአፄ ቱዎድሮስ ላይ ቂም የያዙ ሁሉ መሳፍንት ፈፅመውታል።

ለኦሮምያ ካርታም ያለኝ አመለካከት እንዲሁ ነው፤ በቅርቡ በማሕበራዊ ድረ-ገጽ በቀስቀስኩት ውይይት ላይ ኦሮሞው ጠባብዋን "ኦሮምያን" ሳይሆን ጠቅላላዋን ኢትዮጵያን እንደ ቤቱ ሊያያት ይገባል ብዬ ላቀረብኩት ሀሳብ አንድ የኦሮሞ ብሔርተኛነት አራማጅ "ጠቅላላዋን ኢትዮጵያን "ኦሮምያ" ብለን እንጥራና ይህን አጀንዳ እንዝጋው" ሲል አስተያቱን ሰጥቷል። የዚህን ሀሳብ ተተግባሪነት በኋላ እናያለን፤

አንዳንድ ኦሮሞ ጓደኞቼ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ነገር እንደሌለ እና ኢትዮጵያውያን እንዳልሆኑም ይነግሩኛል። ኦሮሞዎች ኢትዮጵያውያን ካልሆኑ ምን ሊሆኑ ነው ታዲያ? በኔ አስተያት ኢትዮጵያዊነቱን የሚክድ ማንኛውም ኦሮሞ፣ ኦሮሞዎች በ16ኛው ክፍለ-ዘመን በማደጋስካር በኩል ከእስያ የመጡ የውጪ ወራሪዎች ናቸው የሚል ሃሳብ በስህተት ከሚያራምዱ ጋር የሚስማማ ነው። ኦሮሞዎች ከውጪ የመጡ ወራሪዎች ከሆኑ በየትኛው መብታቸው ነው ካንዲት አገር ላይ "ኦሮምያ" የምትባል ግዛት የሚቆርሱት? ያንተ ያልሆነውን ዳቦ እንዴት ትበላዋለህ? ኦሮሞዎችስ ፍፁም ኢትዮጵያውያን ነን። አማሮች፣ አፋሮች፣ ሀዲያዎች፣ ጉራጌዎች፣ ጋምቤላዎች፣ ከምባታዎች፣ ወላይታዎች፣ ሶማሊዎች እና ሁሉም ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵ ልጆች እንደሆኑ ሁሉ ኦሮሞዎችም የኢትዮጵ ልጆች ናቸው። ለኢትዮጵያዊነት ሥነ-ልቡና፣ ለታሪክዋ፣ ለባሕልዋ፣ ለቋንቋዋ፣ ለሥነ-ጽሑፍዋ፣ ለማሕበራዊ ሳይንስዋ፣ ለአንትሮፖሎጂዋ እና ለጆኦግራፊዋ እንደሌሎቹ ዜጎች የድርሻቸውን ብዙ አበርክተዋል። በተጨማሪም ባለፉት 3500 ዓመታት ውስጥ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከልክ በላይ ነው። ይህን ሁኔታ *"ኦሮሞ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያበረከተው አስተዋጽኦ"* በሚለው ጽሁፌ አብራርቸዋለሁ። ምንም እንኳ ወታደሮች እና ቀሳውስት ሆነው የተጫወቱትን ሚና ባለፉት 3000 አመታት ውስጥ ቀላል ባይሆንም በለለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ውስጥ በጋብቻ ገብተው የኢትዮጵያን የታሪክ አቅጣጫ ላለፉት 700 ዓመታት ሲወስኑ መኖራቸው የማይታበል ሀቅ ነው። ይኸውም ለለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት በሸዋ እንደገና ከመሰረተው ከአፃዥ ጫሳ የልጅ ልጅ እና ከጊፍቲ ሀዊ መንዲያ ልጅ ከተስፋ-እየሱስ የግዛት ዘመን ጀምሮ ነው።

ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ አዲስ መጥ ባዕዳን አለመሆናቸውን ይህ በሚገባ ያረጋግጣል። ኦሮሞዎች ባዕዳንም አይደሉም፤ ታሪክ ላይኖራቸው የሚጮሁ ድመቶችም አልነበሩም፤ የታላቁን አባታቸውን የኢትዮጵን ደማቅ ታሪክ አንግበው የሚያገሱ አንበሶች ነበሩ እንጂ። ናቸውም። ኦሮሞዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥረው እዛው ግሩም ድንቅ ታሪክ የሠሩ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የማይቀበል ማንኛውም ኦሮሞ አንድም የገዛ ታሪኩን የማያውቅ ወይም ክቡር ማንነቱን አሽቀንጥሮ የጣለ፥ የሚያሳዝን ሰው ነው።

------------------------//--------------------------

# መደምደሚያ

ከዚህ በላይ በቀረበው ጽሁፍ ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ ባእዳን እንግዶች ሳይሆኑ ልክ እንደ አማራና እንደሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አገር በቀል ኗሪዎች መሆናቸውን ተምረናል። ከዚህም አልፎ ኦሮሞና አማራ በደም የተዛመዱና ላለፉት 3500 ዓመታት በማህበራዊ አኗኗር፣ በባሕል፣ በቋንቋ፣ በሐይማኖትና በመንፈሳዊ ሕይወት የተቀላቀሉ እና የተዋሃዱ መሆናቸውንም አውቀናል። ኦሮሞዎች በኢትዮጵያ አመራር ውስጥ ቁልፍ ሚና የተጫወቱ እና ለኢትዮጵያ ስልጣኔም ጉልህ ድርሻ ያበረከቱ ዜጎች ናቸው። ያበረከቱት አስተዋፅኦም በስነ-ልሳን፣ በፍልስፍና፣ በመንፈሳዊ ባህል በወታደራዊ ሳይንስ፣ በቅኔ፣ በቤተ ክህነት አገልግሎት፣ በዳንኪራ፣ በሙዚቃ እና በእደ-ጥበብ ዘርፎች ተዘርዝሮ ቀርቧል። የኦሮሞና የአማራ ግንኙነት በብዙ መልኮች በርስበርስ መፈቃቀድ፣ መፈቃቀር እና መከባበር ላይ የተመሰረተ እና በርግጥም በአርአያነት የሚታይ መሆኑን ተገንዝበናል። ባለፈው ታሪካቸው ብቻ ሳይወሰኑ ለወደፊትዋም ኢትዮጵያ አንድነት፥ እድገት እና ሰላም ምሰሶ እንደሚሆኑ አልጠራጠርም።

ስለ ኦሮሞና አማራ የዘር ሃረግ ምንጭ ስንመረምር፥ ምንጩ አንድ መሆኑን ተገንዝበናል። ከሌላው ሁሉ ማስረጃ ይበልጥ አንዱ ላይ ብቻ እንኳ ብናተኩር በቂ ነው። ኦሮሞና አማራ በአባይ ዙርያ በጎጃም ከአንድ ምንጭ ለመቀዳታቸው ሶስት የማይነቀነቁ ማረጋገጫዎች አሉ። አንደኛ፥ አበው ኦሮሞዎች ስነፍጥረትና አባታችን (ደሸት) ከውሃ ውስጥ ፈለቀ ብለው ማውጋታቸው፥ ሁለተኛ፥ በዛው በምስራቅ ጎጃም ውስጥ ከውሃ የፈለቁ እነማይ ወይም የውሃዎቹ ሰዎች የሚባሉ አማሮች አሁንም መኖራቸው፥ እና ሶስተኛው ደሸት የሚባል ሰው እና ዘረ-ደሸት የሚባሉ ሰዎች በዛው በጎጃም እንደነበሩ መታወቁ ነው። ለምሳሌ በ *ውዳሴ ማርያም* አንድምታ ላይ ስለ ዘረ-

ደሸት የተመዘገበ ከትውልድ ትውልድ ወደ እኛ የተላለፈ እውነት አለ። በዚህ መፅሃፍ ውስጥ ደሸትን ዘረደሸት ብለው በመጥራት፥ ዘረ-ደሸት ከአባይ ምንጭ አጠገብ ሆኖ በጎሊናው ሲመስጥ፥ ድንግል ማርያም ወደ ፊት የምትወልደውን እየሱስን አቅፋ፥ በእነሱ ላይ ደግሞ እየሱስ ሲወለድ ወደ ፊት የኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ ወጥታ የደሸትን ልጆች ሰብአስገልን ወደ ቤተልሄም የምትመራቸውን ኮከብ በቅድሚያ ዐያት። እሱ የዐያትን ኮከብ ከዐያት ከ 1600 ዐመታት በሁዋላ እውነትም ከኢትዮጵያ በተጨማሪ፥ ሱዳን እና የመን ይደርስ የነበረው የኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ ታየች። በአፄ ባዜን ንጉሠነገሥትነት ስር በዛን ጊዜ 12 ነገሥታት የነበሩት የደሸት ልጆች ወንድማማቾች የኦሮሞን፥ የአማራን፣ የትግሬን እና የሌሎቹንም ጎሳዎች ወክለው፥ የኢትዮጵያን ቢጫ ወርቅ፥እጣን እና ከርቤ ይዘው፥ በኮከብዋ እየተመሩ ወደ ቤተልሄም አምርተው ለህፃኑ መሲህ ለእየሱስ ክርስቶስ ገፀበረከት አቅርበዋል። ለምሳሌ ከኦሮሞ ንገሦች አንዱን፥ ከአማራዎቹ ደግሞ ዐራቱን በስም ለመጥቀስ ያህል ኦሮሞው፥ የደርዲና፥ የሰገል፣ የኦርመን (የኦሮሞ)፥ እና የማጂ ንጉሥ፥ አማሮቹ የጎጃም እና የጣና ውስጥና ዙሪያ፥ በደሸት ከተማ ተቀማጭነት የጎንጂ እና ጉንዳጉንዲት ነገሥታት አጎጃ ጀባን፤ አበል፤ቶና እና በረካ ነበሩ። የኦሮሞው ንጉስ መጋል ወደ ቤተልሄም ከመጓዙ በፊት የመደባይ-ኦሮሞ ካህናትን ይዞ እና የኦሮሞ ወታደሮችን ከተት ብሎ፣ በአፋሮች ድንቅ መርከብ ተሳፍሮ፥ ባህር ተሻግሮ፥ ስፔንን እና ፖርትጋልን ቀኝ እንደ ገዛ እዚህ ፅሁፍ ከላይ መቀመጡን ተገንዘበናል። እንግዲህ እውነተኛው እና ትልቁ ታሪካችን ይህንን ይመስላል። ይህም ሲባል፥ ዘመዳሞቹ ኦሮሞዎችና አማሮች ባለፈው ታሪካቸው ብቻ ሳይኩራሩና ሳይገቱ፥ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋራ በመተባበር ለወደፊትዋ ኢትዮጵያ አንድነት፥ እድገት እና ሰላም ምለሶ እንደሚሆኑ አልጠራጠርም።

# Notes:

## The True Origin of the Oromo and Amara


1. Getachew Haile, *Ye Aba Bahriy Dersetoch,* p. 76.

2. Bairu Tafla. *Asma Giyorgis and His Work,* p.308.

3. Bairu Tafla. ibid., p. 309.

4. Bairu Tafla. ibid., p. 311.

5. Bairu Tafla. ibid. p. 138.

6. Aleka Taye Gebremariam, *Ye Ethiopia Hizb Tarik,* pp. 60-61.

7. Tekle Tsadik Mekuria, Ke Atse Libine-Dengil Iske Atse Tewodros, p. 94

8. Yilma Deressa, Ye Ethiopia Tarik Basra Sidestengaw Kifle Zemen,pp. 214-215.

9. Mohammed Hassen, T*he Oromo of Ethiopia*, p. 4

10. Getachew Haile. ibid., pp. 26-27.

11. Bonnie K. Holocomb and Sisai Ibssa, *The Invention of Ethiopia ,p.5.*

12. Harold Marcus. *A History of Ethiopia,* pp. 34-35.

13. Tekletsadik Mekuria, ibid., p. 9.

14. Bairu Tafla, ibid., p. 204.

15. Bairu Tafla, ibid., p. 879.

16. N.Y, Saturday, October 21, 2006.

17. Aman Belai, Metsehafe Abrihit, p. 490-492.

18. Bairu Tafla. ibid., p.202.

19. Merigeta Lisane Work Gebre Giorigis, *Tintawi Sirate Mahlet Ze Abune Yared Liq,*

pp. 14-16.

20. Aman Belai, *Metsehafe Subae Ka'le*. p. 309.

21. Aman Belai. Ye Tintwa Ye Ethiopia Tarik. p. 350.

22. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik. p. 41.

23. Aman Belai, .ibid. p. 43.

24. Aman Belai. ibid. p. 57.

25. Aman Belai, pp. 306-308.

26. *Strong's Greek Lexicon*. #2739 and #4028, available on line.

27. Psalm 68: 31.

28. Aman Belai, Ye Tintwa Ethiopia Tinsae Tarik, p.10

29 Aman Belai. Metsihafe Subae Zebeaman Kale, pp. 320-334.

30. Aman Belai. ibid., p.324.

31. Psalms, 72:10.

32. Aman Belai, locit., p. 324.

33. Getachew Haile, ibid., p.76.

34. G.W.B. Huntingford, in *The History of The Galla of Ethiopia,* p.12.

35. Aman Belai. Hizbaw Kedamawi Mestawet Tarik, p. 28.

36. *The Holy Bible,* Numbers 21, 14.

37.Bairu Tafla, Asmagiyorgis and His Works, p. 310.

38. Aman Belai. Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, p. 30.

39. Aman Belai,*Metsihafe Abrihit,* p.479.

40. Aman Belai. Ye Tintwa Ethiopia Tinsae Tarik. p. 202.

41. Aman Belai. Ye Tinatwa Ethiopia Negestat Tarik, pp. 53-55.

42. Aman Belai, *Metsehafe Abrhit,* p. 4.

43. Ye Ethiopia Tarik, Ke Atse Libine-dengil iske Atse Tewodros, p. 21

44. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, p45.

45. Aman Belai. *Yetintwə Ethiopia Tinsae Tarik,* p.320.

46. Belai, Aman, Metsehafe Subae, p.59.

47. Aman Belai, *Metsehafe Abrihit*, p.308.

48. Aman Belai, ibid., pp.485-487.

49. Aman Belai, Metsihafe Subae Zebemaman Kale, pp.127-128.

50. Bairu Tafla, Asma Giyorigis and His Works, p. 202.

51. Aman Bela. *Mtesehafe Abrhit*, p. 521.

52. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, pp. 34-35.

53. 101 Psalm 110, 4

54. Aman Belai. Mesehafe Subae Kale Zebeaman, pp. 58-59

55. Aman Belai, ibid. p. 309.

56. Psalms 68: 31.

57. Numbers, 10, 29--32

58 Luke, 11, 32.

59. Fikre Tolossa, The Hidden and Untold History of the Jewish People and

Ethiopians, pp.39-43)

60. Aman Belai. *loc.cit. pp.*129, 150-152.

61. Aman Bela.loc.cit., p.128.

62. Aman Belai, loc.cit., pp.151-152.

63. Aman Belai, Ye Tinantinawa Ethiopia Tarik, p.199.